# የጋዜጠኞች መፈታት፣
# ብቻውን ዘላቂ መፍትሄ አያመጣም

April 12, 2007

በኢትዮጵያ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት እንዲረጋገጥ፣ የተከፈለው መስዋእትነት፣ ብዙ ትውልዶችን አስቆጥሯል። የኢትዮጵያ ህዝብ ህሳቡን በነጻነት መግለጽን ባህል እንዲያደርግ፣ ከእስራት ጀምሮ የህይወት መስዋእትነት ጭምር ተከፍሏል። በተለይም ይህ ትውልድ ሃሳቡን በነጻነት ለመግለጽ የብዕር ጠመንጃውን አንግቶ፣ የህዝብን ድምፅ ለማሰማት ታስሮና ሞቶ፣ ታላቁን የአርበኝነት ተግባር ፈጽሟል፣ ወደፊትም ይፈጽማል።

ህዝብ የማወቅ መብቱ በተፈጥሮ የተለገሰው ፀጋ ነው። ከህዝብ አብራክ የወጣ ጋዜጠኛም ለዚህ የህዝብ መብት ሳያወላውል ይቆማል፣ ለቆመለት አላማም ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል ምንግዜም ዝግጁ ነው። ለእውነትና ለህዝብ መብት በመቆም የሚመጡ እስራት፣ ስደትና ሞት ለጋዜጠኛ ሹመትና ሽልማቱ እንጂ፣ እንደመከራ የሚቆጠሩ አይደሉም--- ከቶውኑ።

ለዚህም ነው፣ ባለንበት ዘመን ከህዝብ አብራክ የተወለዱ የብዕር አርበኞች፣ ራሳቸውን እስከሞት ለሚያደርስ መስዋእትነት አዘጋጅተው የሚታገሉት። ለዚህም ነው፣ እስራትና ስደት ሳይበግራቸው፣ ነፍሳቸውን በሞት አቁማዳ ከሽፈው በጽናት የቆሙት። ለዚህም ፅናታቸው አኩሪውን ተግባር የፈጸሙት፣ በመከራቸው ጊዜ ያጽናኗቸውና የደገፏቸው ኢትዮጵያዊያንና የአለም አጋሮቻችን በመሆናችው፣ የኩራቱ ባለቤት ሁሉም ህዝብ ነው። በመሆኑም ስለህዝብ ብለው በመታሰር እለተ-ሞታቸውን ይጠብቁ የነበሩ ጥቂት ጋዜጠኞች መፈታትቸው፣ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አስተዋጽኦ ውጤት መሆኑ መዘንጋት የለብትም። ለዚህም ገንዘባቸውንና ጊዜያችውን ለሰዉት፣ በስላማዊ ሰልፎችና ባገኙት አጋጣሚ ድምጻቸውን ያሰሙትን በሙሉ፣ በተፈቱት ጋዜጠኞችና ቤተሰቦቻቸው ስም ከልብ እናመሰግናለን።

ሆኖም መዘንጋት የሌለብን ጉዳይ አለ። ዛሬም ቢሆን፣ ስለአገራቸውና ስለህዝባቸው ብለው የታሰሩ፣ በየእለቱም የመከራን ግፍ የሚቆጥሩ የህሊና እስረኞች መኖራቸውን ለአንድ አፍታም መርሳት አይኖርብንም። ይልቁንም በአንድነት ቆመን በመጮሃችን፣ ተባብረን ድምጻችንን በማሰማታችን፣ ያገኘነውን መልካም ውጤት ተመልክተንዋልና... ዛሬም በእስር ላይ ያሉትን የፖለቲካ እስረኞችና ጋዜጠኞች ለማስፈታት የምናደርገውን ጥረት ሳንሰለስ መቀጠል ይኖርብናል።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የጥቂት ጋዜጠኞቻችን መፍታትና ከቤተሰባቸው ጋር መቀላቀል ደስ ቢያሰኘንም፣ የጥቂቶች መፈታት ግን ለአገራችንና ለህዝባችን ዘላቂ የሆነ፣ የሰላምና የብልጽግና መፍትሄ እንደማያመጣ፣ ጽኑ እምነት አለን። በጥቂት ጋዜጠኞቻችን መፈታት ሳቢያ የፍትህ አካላቱ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ናቸው የሚል ብዥታ የለብንም። የፍትህ እና የነጻነት ግማሽ የሌለው በመሆኑም...

1ኛ- የተቀሩትን ጋዜጠኞችን ጨምሮ ሁሉም የህሊና እስረኞች መፈታት ይኖርባቸዋል።
2ኛ- ከኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች የተወሰዱት ንብረቶች፣ ከሞባይል ስልክ ጀምሮ ገንዘብና ኮምፒዩተሮችን ጨምሮ ሌሎች የግል ቁሳቁሶች ሊመለሱላቸው ይገባል።
3ኛ- የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞችና የማህበሩ ቢሮ እንደገና ተከፍቶ ስራቸውን መጀመር፣ የማህበሩም ንብረት ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የንብረቱ ባለቤት ለሆነው አካል መመለስ አለበት።
4ኛ- ያለምንም አድልዎ፣ ሁሉም የሃይል ወገን በእኩልነት ላይ በተመሰረተ መንፈስ፣ ሙሉ ለሆነው ፍትህና ነፃነት ተባብሮ እንዲቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ከዚህ ውጪ ግን የጥቂት ጋዜጠኞች መፈታት ዘላቂ መፍትሄ እንደማያመጣ ሁሉም ወገን ተገንዝቦ፣ በጊዜያዊ ድል ሳንዘናጋ አሁንም የታሰሩትንና የሚንገላቱትን የህሊና እስረኞች... በጸሎት እናስባቸው፣ በተግባር እንደግፋቸው፡፡

የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር
ፕሬዘዳንት ክፍሌ ሙላት

በስደት የሚገኙ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ስብሳቢ
ዳዊት ከበደ